# አዋጁ ብርታት የሚሆነው ለበጎዎቹ ነው

አማረ ኢ.

ባሳለፍናቸው ጥቂት ሳምንታት ሁለት ተቃራኒ አመለካከቶች በየፊናቸው ጎራ ለይተው ለሞቀ ክርክር እንዲበቁ የዳረገ አንድ ትልቅ አዋጅ ፀድቆ ሥራ ላይ ውሏል። አዋጁ ከመፅደቁ በፊት የሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት፣ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችና ሌሎችም በቂ ምክክር አድርገውበታል። ይሁንና መከራከሪያ ነጥቡ አሁንም የሙቀት ግለቱ አይሎ ቀጥሏል። የአገር ውስጥና ጉዳዩ የማይመለከታቸው የውጭ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀን ጭምር አጀንዳ ሆኖ እየተራገበ ይገኛል አዲሱ የበጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ።

አዋጁን በተመለከተ በሁለቱ ጎራዎች ማለትም በአንድ በኩል መንግስት በሌላ በኩል ደግሞ ያገባናል የሚሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በሌላ ጎራ ተሰልፈው እየተከራከሩ ይገኛሉ። በመካከላቸው የማይታረቁ ቁልፍ ጉዳዮች እንዳሉዋቸውም ከሚያነሱዋቸው የክርክር ነጥቦች መገንዘብ ይቻላል። እኔም ከሚነሱ በርካታ የመከራከሪያ ነጥቦች መካከል ሁለት ጉዳዮች ላይ የግል አስተያየት ለመስጠት ተነሳሳሁ።

የአንድን አገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልጽግና በዘላቂነት ለማረጋገጥ ከሚጠቀሱ ጠቃሚ ግብአቶች መካከል አንዱ በራሱ የሚተማመን ዜጋ የማፍራት ጉዳይ ነው። ለምን ቢባል በራሱ የሚተማመን ዜጋ ለአገሩ ደህንነትና ህልውና ተቆርቋሪ፣ ስራ ፈጣሪ፣ የለውጥ ሀዋሪያ ከመሆኑ ባሻገር ድህነትን ለማጥፋት የታቀዱ አዋጆችንና ፖሊሲዎችን በቆራጥነት በመተግበር የብልጽግና ጉዞውን የማቀጣጠልና የማፋጠን ጉልበት ያለው ሀይል ጭምር በመሆኑ።

ከዚህም በተጨማሪ በራሱ የሚተማመን ዜጋ ለዘላቂ ልማት መረጋገጥና ለዲሞክራሲያዊ ስርአት መስፈን የማይተካ ሚና አለው። እንዲሁም በዜጎች መካከል ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል በተቻለ መጠን እንዲኖር ያስችላል።

ታዲያ ይህን መሰሉን ሀይል ለማፍራት ትክክለኛ የአደረጃጀትና የተመቻቹ ኢኮኖሚያዊ ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል። ከዜጎች ውስን አቅም በመነሳት ደረጃ በደረጃ የተሻለ ጉልበት ለመፍጠርም ሌሎች ተጨማሪ ህጎችና ማእቆፎችን የማዘጋጀትና ካሉም ወቅታዊነታቸውን በመፈተሽ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ሀላፊነት ከሚሰማው መንግስት የሚጠበቅ ተግባር ነው።

ዜጎች ያላቸውን ሀብት በአግባቡ ተጠቅመው አስተማማኝና ቀጣይነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥና ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት ትናንትም ሲያደርጉት የነበረ ዛሬም ያለ ተግባር ነው። መብቶቻቸውን ለማስከበርና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎቶቻቸውን ለሟሟላት ከውጭ የገንዘብ እርዳታ ሳይደረግላቸው ለረዥም ዘመናት በተለያዩ አደረጃጀቶች ታቅፈው ሲንቀሳቀሱ እንደነበሩ ሩቅ ሳንሄድ እቁብና እድሮችን በአብነት ማንሳት ተገቢ ይሆናል።

ታድያ አሁን ከአዲሱ አዋጅ መጽደቅ ጋር ተያይዞ ካለ የውጭ የገንዘብ ድጋፍና እርዳታ የልማት ስራዎቻቸው ይደናቀፋሉ፣ የዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ መድረክ ይጠባል ተብሎ የመከራከሪያ አጀንዳ መቅረቡ ለምን ይሆን?

እውነት በኢኮኖሚ አቅም ውስንነት ምክንያት የዜጎች የልማት ጉዞ ይደናቀፋል የሚል እምነት ከተያዘ ከውጭ በህዝብና በአገር ልማት ስም በልመና የመጣው በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እስከአሁን ድረስ ምን ተሰራበት? 3ሺ737 ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በህዝብ ስም ካሰባሰቡት ገንዘብ መሬት ላይ ወርዶ ህዝቡ ተጠቃሚ የሆነበት ምን ያህል ይሆን?

ከዚህ ይልቅስ የጥቂቶችን ኪስ በማድለብ እንዲመፃደቁ ከማድረግ በተጨማሪ ወጣቱ ትውልድ ከስራ ፈጣሪነት ይልቅ የልመና እጁን በመዘርጋት በራስ የመተማመን መንፈስ ርቆት በየሚዳው እጁና እግሩን አጣጥፎ እዲቀመጥ በማድረግ የተረጂነት ስሜት እንዲዳብር የበኩላቸውን አሉታዊ ድርሻ ተጫውተዋል- ከተወሰኑት ለልማት ከቆሙ ድርጅቶች በስተቀር።

አዲሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ በግልጽ እንዳስቀመጠው በአገሪቱ በመካሄድ ላይ ያሉትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስራዎችን በትክክል ለመደገፍ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን የሚያበረታታ እንጂ የሚያንኳስስ አይደለም።

በአገሪቱ የሚከናወኑትን የዜጎች ልማት ለመደገፍ በሚሹ ድርጅቶች ውስጥ ተጠያቂነትና ግልጽነት ይስፈን መባሉ የት ላይ ነው ስህተቱ? በእርግጥ ስህተት የሚሆነው አላማቸውን ስተው በዝርፍያ ላይ በተሰማሩ አካላት አይን ሲታይ ብቻ ይሆናል። ስሕተት የሚሆነው በዘመድ አዝማድ፣ በወዳጅነትና በእከከኝ ልከክልህ መርኅ ተሰባስበው በሚቀራመቱ ዓይን ሲታይ ነው።

ሁለተኛ መከራከሪያ ነጥብ ሆኖ የሚነሳው አዋጁ የዜጎችን የፖለቲካ ተሳትፎ መድረክ ያጠባል የሚለው እውን ህገ መንግስታዊ መሰረት አለውን?

የፖለቲካ ተሳትፎ መድረክ ጠቧል ሊሉ የሚሞክሩት ሃሳቡን ከሚያራምደው የማኅበራዊ ሳይንስ ሊቅና ፈላስፋ ጀርገን ሃበርማስ በተሳሳተ መንገድ ቆንፅለው እንደሆነ ለመረዳት ችለናል።

በመሠረቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ80 በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሉበት ሁኔታ፣ ከዚህ አደረጃጀት ውጭ ደግሞ በርካታ ልዩ ልዩ ማኅበራት በሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ፣ ዜጎች በፈለጉበት መንገድ የመደራጀታቸው ሁኔታ መብት በሆነበት አገር የፖለቲካ መንቀሳቀሳሻ ወይም መላወሻ ሥፍራ ያሳጣል ማለት ሆን ብሎ ዕውነታውን ለማጣመም ከመሞከር ውጭ ሌላ ሊባል አይችልም።

ዛሬም ቢሆን መንግሥትም ሆነ አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ያደረገው አዋጅ ለሕዝቡ ትምህርት ቤት የሚገነቡ፣ ጤና ተቋማት አቋቁመው ሕዝቡ እንዲያስተዳድራቸው የሚያደርጉ፣ መስኖ ገንብተው የአርሶአደሩን ጥረት የሚደግፉ ድርጅቶችን ወዘተ ያበረታታል፣ ይሸልማል፣ አርአያነታቸውን መጥቀሱን ይቀጥላል።

በህገ መንግስታችን ከአንቀጽ 29 እስከ 44 ድረስ እንደተቀመጠው የዜጎች በተለያዩ የፖለቲካ መድረኮች መሳተፍና መደራጀት የዜጎች የራሳቸው መብት ነው። በዜጎች ፍላጎት፣ ጥረትና የገንዘብ አቅም የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብታቸው በሕገ መንግሥት የተከበረና መንግሥት ሊሰጣቸውም፣ ሊከለክላቸውም የሚችለው ጉዳይ አይደለም።

ዜጎች ለመብታቸው ለመሟገት የውጭ ገንዘብ የማያስፈልጋቸው ከመሆኑ በላይ የውጭ ገንዘብ ሳያገኙ ለዘመናት ለመብታቸው በተለያዩ አደረጃጀቶች ታቅፈው ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል፤ አሁንም ተደራጅተው የመንቀሳቀስ መብታቸው የተጠበቀ ነው።

እነዚህን መብቶች ለማስከበር የሚያስችሉ የህግ ማእቀፎችን የማውጣት ሀላፊነት ደግሞ የሕግ አውጭው እንጂ የውጭ ሀይሎች ጉትጎታና የበጎአድራጎት ተቋማት ተግባር አይደለም። የውጭ ሀይሎች ጉትጎታና የበጎአድራጎት ተቋማት ተግባር ነው ከተባለ ግን ይህን የሚል ወገን ሉአላዊነት አልገባውም፣ ወይም ጥቅም አውሮታል። ስለዚህ መከራከሪያ ነጥቡ ህገመንግስታዊ መሰረት ከቶ እንደሌለው ያሳየናል።

በአጠቃላይ አዲሱ አዋጅ ዜጎች የሚያከናውኗቸውን የተለያዩ የልማት ስራዎችን መደገፍ አላማቸው ያደረጉ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተግባራቸውን ይበልጥ አጠናክረው እንዲቀጥሉበት ብርታት የሚሰጥ ሲሆን በእርዳታ ሽፋን የልማትና የዲሞክራሲ መሰረት የሆኑ ምሰሶዎችን የማፍረስ ድብቅ አላማ ያላቸውን ቅስም የሚሰብር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። አዋጁ በጎ የልማት ሥራዎችን ለሚያከናውኑ ብርታት መሆኑን ይቀጥላል።

አበቃሁ።